# የዜጎች መድረክ

ቅፅ 1 ቁጥር 48 ሐምሌ 25 ቀን 2012 ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## “የሕዝቡን ጠብቀኝ የሚለውን ጩኸት የቁራ ጩኸት ያደረገውና ሕዝቡን መጠበቅ ያልቻለው መንግሥት መጠየቅ አለበት ! ”

አንዷለም አራጌ የኢዜማ ምክትል መሪ-ቡብ ነገር



# መንግሥት የሕግ የበላይነትን ያስከብር የሚለው የሕዝብ ጥያቄ የመጨረሻ መሆን አለበት

ሐምሌ 25/2012 ዓ.ም አዲስ አበባ



የሕዝብ ጥያቄ የአገር ህልውና የዜጎች ደህንነት ይከበር ተዋደን ተዋልደን በኖርንበት አገር እንደ ባይተዋር መሆን በስጋት መኖር የለብንም የሚል ከሆነ ውሉ አድሯል::

ይህ ጥያቄ ሲጠየቅም ጊዜያዊ ፀጥታ ማስጠበቅም ሆነ ዘላቂ ሰላም ማስፈን የመንግስት ብቸኛ ስልጣን መሆኑን በማመን ነው:: አንድ አንድ ጊዜ ይሄ የሁሉም ድርሻ ነው እየተባለ ሲገለጽ ይደመጣል:: ትክክል አይመስለኝም:: የዜጎች ድርሻ ሕግን አክብረው መኖር ነው:: ማስከበር ግን የመንግሥት ስልጣን ኃላፊነትም መሆኑ ግልጽ ሊሆን ይገባል:: ለመንግሰት ይህን ኃላፊነትን ተወጣ ብሎ መንገርም ተገቢ አልነበረም ::

መንግስት ይህን ኃላፊነቱነ ሲጠየቅም ሆነ ሲከሰስ የሚያቀርባቸው ሐሳቦች በምንም መመዘኛ ተቀባይነት አይኖራቸውም:: ምክንያቱም የመጨረሻው ሃይልን የመጠቀም ብቸኛ መብት (Monopoly of Power) የመንግስት ብቻ በመሆኑ ነው:: ይህ ሳይሆን ቀርቶ ለተራዘመ ጊዜ ዜጋው በተናጠልም ሆነ በቡድን ራስ ወደ መከላከል ሕግን ወደ ማስከበር ኃይል ወደ መጠቀም ከገባ የኃይል መከፋፈል (Anarchy) ውስጥ ገባን ማለት ነው:: ይህ ደግሞ የአገር መፍረስ አደጋን ያመጣብናል:: በሌሎች በፈረሱ አገሮች እንደታዘብነው በራሳችንም እንደተፈተነው የአገር መፍረስ

> ‹‹ መንግስት ለእነዚህ የአገርና የዜጎች ቁስሎች የሚሰጣቸው ምላሽ ደግሞ እጅግ የሚያበሳጩና ኃላፊነቱን የዘነጉ ናቸው:: የህግ የበላይነት ይከበር ብሎ ሕዝብ በስፋት ለሚያነሳው ጥያቄ አንዱ የሚያሳዝነው ምላሽ ወደ አምባገነንነት አትግፉን የሚል ነው::››

የአመታት ወይም የወራት ሳይሆን የቀናት ወይም የሰዓታት የሕግ የበላይነት መጥፋት ይበቃዋል::

በግልጽ ለማስተዋል እንደቻልነው አገር ፈርሰ ማለት ህዝቡ ፈረሰ፣መሬቱ ተደረመሠ ማለት ሳይሆን የሕግ የበላይነት ተጣሰ ማለት ነው።ከላይ የገለጽናቸው በፈረሱት አገሮች አብዛኛው ሕዝብ አሁንም አገር ውስጥ ▶



▶ አለመሬቱም የፈራረሱ ከተሞችን ይዞ አለ።አገሮች አብዛኘው ሕዝብ አሁን አገር ውስጥ አለ።አገሮቹ የፈረሱት የሕግ የበላይነት በመጥፋቱ መዕከላዊ መንግስት በመዳከሙ ስልጣኑ በጎበዝ አለቃ በመሸርሸሩ ነው::

በአገራችን በአለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ብቻ የህግ የበላይነትን የሚሸረሽሩ የሀገርን ህልውናና የዜጎችን የደህንነት አደጋ ላይ የጣሉ በርካታ ሕገ ወጥ ክስተቶች ነበሩ ለእነርሱ በቂ ምላሽ ባለመስጠቱ ዛሬ እዚህ ስጋት ላይ ሆነ የማዕከላዊ መንግስት የፀጥታ መዋቅር የዜጎችን ሕይወትና ንብረት መጠበቅ አደጋ ሲመጣ ቀድመው በማክሸፍ ማዳን ሲገባቸው ታሪክ ይቅር የማይለው ስህተት ፈጽመዋል:: እስከ አሁን በክልም ሆነ በፌደራል ይቅርታ የጠየቀም ሆነ ኃላፊነቱን የለቀቀም አለመኖሩም እጅግ ያሳስባል::

ለመሆኑ የስንት ዜጎች ሕይወትና ምን ያሕል የአገር ንብረት ሲጠፋ ነው ምህዳሩ ሰፍቷል የሚባለው?የሕግ የበላይነት

> ‹‹ በውጭ ወራሪም ሆነ በውስጥ ቦርቧሪ የሚደርስብንን ፈተና የመቋቋም ልምድ አለን::››

ወደቅን:: ቀደም ሲል በአዋሳ፣ በሻሸመኔ፣ በበደሌ፣ በባሕር ዳር፣ በአዲስ አበባ፣ በቡራዩ በዩኒቨርሲቲዎች ወዘተ ለተፈጠሩ ችግሮች አስተማሪ እርምጃ ባለመወሰዱ እና ተጎጂዎች ፍትህ ባለማግኘታቸው ችግሩ ቀጥሏል ብቻ ሳይሆን እየባሰ መጥቷል:: ዜጎች የመንግስትን ሕግ የማስከበር አቅምና ፍላጎት ጥያቄ ውስጥ አስገብተውታል ይህም ደግሞ አደገኛ ደረጃ ነው::

መንግስት ለእነዚህ የአገርና የዜጎች ቁስሎች የሚሰጣቸው ምላሽ ደግሞ እጅግ የሚያበሳጩና ኃላፊነቱን የዘነጉ ናቸው:: የህግ የበላይነት ይከበር ብሎ ሕዝብ በስፋት ለሚያነሳው ጥያቄ አንዱ የሚያሳዝነው ምላሽ ወደ አምባገነንነት አትግፉን የሚል ነው:: መንግስት ሕግን የማስከበር ኃላፊነት ከአምባገነንነት ጋር ምንም ዝምድና የለውም።በጣም ብዙ ዲሞክራሲያዊ አገሮች ህግ የበላይነት በማያወላዳ መልኩ ሲያስከብሩ እያየን ነው:: ስለዚህ የሕግ የበላይነት የማስከበር ኃላፊነት ሲነሳ ሮጦ ወደ አማባገነንነት ማማተር የመንግስትነትን ሚና በትክክል አለመረዳት ከዚያም አምባገነንነት ኢትዮጵያ ውስጥ ሕዝብ የማይቀበለው ወጣቱ ከትከሻው ላይ ያሽቀነጠረው ደግሞም ሊሸከመው የማይፈቅደው መሆኑም መዘንጋት ይመስለኛ:: ለዚህም ነው በቶሎ መታረም አለበት የምለው ::

ሌላው ስለ ህግ የበላይነት ሲነሳ የሚሰማው ዲስኩር የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋት እየታገስን በሆደ ሰፊነት እያለፍን ነው የሚል ነው :: ይህንን ገለጻ ከፖለቲካ ነጻ ናቸው ከሚሉት የፍትህ እና የፀጥታ ተቋማት ስንሰማ ደግሞ እጅግ ያመናል የየአካባቢውም ሳይከበርስ ምህዳር ማስፋት የሚባል ቀልድ ይሰራል ወይ በእኔ እምነት የዚህን አይነት ንዝህላልነት የፖለቲካ ምህዳሩን ከማስፋት ይልቅ ጥርቅም አድርጎ የሚዘጋ ነው።ስለሆነም የፖለቲካ ምህዳርን ለማስፋትም የሕግ የበላይነትን ማስከበር ግድ ይላል::

ኢትዮጵያ በብዙ አገዛዝ ስርዓቶችና ፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ አልፋለች ::አሁን ያለንበት ሁኔታም የሚታለፍ አይደለም።በውጭ ወራሪም ሆነ በውስጥ ቦርቧሪ የሚደርስብንን ፈተና የመቋቋም ልምድ አለን::

ዛሬም የወራሪና ወረርሽኝን፣ችግኝ እና ግድብ ብቻ ሳይሆን የሕግ መከበርን በተመለከተ በጋራ የምንቆምበት ወሳኝ ጊዜ ላይ እንገኛለን።መንግስት ሕግን ያስከብር ዜጎች በሕግ መከበር ይተባበሩ።በያለንበት በሕግ አምላክ እንበል።የሕዝብ መንግስትን የሕግ የበላይነትን ያስከብር የሚለው ጥያቄ ዛሬ ለመጨረሻ ጊዜ መሆን አለበት እስከአሁን ያየናቸው ክስተቶች ከበቂ በላይ ትምህርት ሰጥተውናል ብዬ አምናለው:: ስለሆነም ለመጨረሻ ጊዜ እንጠይቃለን:: የሕግ የበላይነት ይከበር የዜጎች በአገራችው ወጥቶው የመግባት ሰርቶ የመኖር ዋስትና ይረጋገጥ::

ኢትዮጵያ በክብር ለዘላለም ትኑር

የሺዋስ አሰፋ

አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

ሐምሌ 25 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# "የሕዝቡን ጠብቀኝ የሚለውን ጩኸት የቁራ ጩኸት ያደረገውና ሕዝቡን መጠበቅ ያልቻለው መንግሥት መጠየቅ አለበት ! "

## አንዷለም አራጌ የኢዜማ ምክትል መሪ

የዛሬው እንግዳችን የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) ምክትል መሪ የሆኑት አንዷለም አራጌ ናቸው፡፡ በወቅታዊ የሀገራችን ፖለቲካዊ ጉዳዮችና በፖለቲካ ትኩሳቶቻችን ዙሪያ ከእሳቸው ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡ መልካም ንባብ!



**የአርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳን ግድያ በምን መልኩ ነበር የሰሙት? ሲሰሙትስ ወደ አእምሮት ምን ነበር የተመላለሰው? ምን ስሜት ፈጠረቦትስ?**

አርቲስቱ መገደሉን የሰማሁት ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም ከጠዋቱ ሁለት ሰአት አካባቢ ነው፡፡ ምንም እንኳ አርቲስቱ የሞተው ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም ምሽት ላይ ቢሆንም የሰማሁት በንጋታው ነው፡፡ ባለቤቴ ወደ ስራ ልትሄድ ስትል ስልክ ተደውሎላት ረብሻ ስላለ እንዳትወጪ ሲሏት ነው የአርቲስቱን ግድያ ልሰማ የቻልኩት፡፡ ያልጠበኩት ነገር ስለነበር ድፍን ያለ ስሜት ነው የተሰማኝ፡፡ ከመደንገጤ የተነሳ ምንም አላልኩም፡፡ በወጣትነት ሕይወቱ በመቀጠፉና በተለይም ሕፃናት ልጆች አባት እንደ መሆኑ መጠን ስሜቴ በጣም ነው የተጎዳው፡፡

**ከአርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳ ግድያ ጋር በተያያዘ የበርካታ ዜጎች ሕይወት ተቀጥፏል፡፡ የበርካታ ዜጎች ንብረትም ወድሟል፡፡ ለዚህ ሁሉ ኃላፊነቱን መውሰድ ያለበት መንግሥት ነው፡፡ ምክንያቱም ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ ቀውሶች ተፈጥረዋል፡፡ የኦነግ የመስከረም 4 ቀን 2011 ዓ.ም አቀባበል እንዲሁም አንድ ግለሰብ"ተከበብኩ"ብሎ ለደጋፊዎቹ ጥሪ ባቀረበበት ወቅት በርካታ ዜጎች ሕይወት ተቀጥፏል፡፡ መንግሥት ከእነዚህ ክስተቶች ትምሕርት በመውሰድ አርቲስቱ ከተገደለ በኋላ የዜጎች ሰላምና ደሕንነት ማስጠበቅ ይገባው ነበር፡፡ ነገር ግን መንግሥት ቀውሱን እንዴት አድርጎ መቆጣጠር እንዳለበት ስላላወቀ ከባለፉት ቀውሶችም ስላልተማረና የዜጎችን ደሕንነትና ሰላም ማስጠበቅ ስላልቻለ መንግሥት ተጠያቂ መሆን አለበት በሚል መከራከሪያቸውን የሚያቀርቡ ወገኖች አሉ፡፡ የእነዚህን ወገኖች መከራከሪያ እንዴት ይመለከቱታል?**

አሁን ያለንበት ዘመን የተለየ ዘመን ነው፡፡ ችግሮቹ የተወሳሰቡ መሆናቸውን እረዳለሁ፡፡ በእኛ (በኢዜማ) በኩል ከሁለት ዓመት በላይ የመንግሥትን ችግር ለመረዳት ሞክረናል፡፡ መንግሥት በእግሩ እንዲቆም (መከላከያውን እስኪቆጣጠር) ጠቅላይ ሚኒስትሩም ኮርቻው ላይ ተደላድለው ለመቀመጥና ውሳኔ እንዲያስፈፅሙ ጊዜ ያስፈልጋቸዋል የሚል አመኔታ ነበረን፡፡ ሌላ ስም እየተሰጠንም ሕዝቡ ትዕግስት እንዲያደርግ፣ እንዲረዳቸውና በእሳቸው ጫማ ውስጥ ለመቆም እንዲሞክር ስንመክር ቆይተናል፡፡ ይህንን ያደረግነው እውነታው እንደዛ ነው ብለን ስላመንን ነው፡፡ አንተ ያነሳሀቸው ግጭቶች ብቻ ሳይሆኑ ከዛም በሰፋ



መልኩ ባለፉት ሁለት ዓመታት ሀገሪቷ ደም ሲፈስባት ሕይወት ሲቀጠፍባት ነበር፡፡ ችግሮች ሲፈጠሩ የመከላከል ከዛም በኋላ ሕዝብን በሚያረካ ሁኔታ ችግር የሚፈጥሩትን ወደ ሕግ የማቅረብና ውጤቱንም ለሕዝብ የማሳወቅ ነገር አይታይም፡፡ በዚህ ላይ በግሌ ቅሬታ አለኝ፡፡ ፓርቲያችንም ተገቢ ነው ብሎ አያምንም፡፡ መንግሥት በሕግ የበላይነትና በሆደ ሰፊነት መካከል ያለውን ደረቅ መሬት እንዲፈልግ ቀድመን ተናግረናል፡፡ ሌላው ስንወተውተው የነበረውና መንግሥት ሊሰማን ፍቃደኛ ሳይሆን የቀረው የካድሬው መዋቅሩ ጉዳይ ነው፡፡ ይህን የካድሬ መዋቅር ማፍረስ ወይንም እነሱ በሚሉት አስተሳሰብ ማዘመን እንደሚያስፈልግ ደጋግመን ነግረናቸዋል፡፡ ይሄንንም ምክራችንን ጆሮ ዳባ ልበስ ብለው አልፈውታል፡፡ ራሳቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከትላንት በስቲያ (ሐምሌ 22 ቀን 2012 ዓ.ም) ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር ባደረጉት ንግግር "አብዛኛው ሌባ እኛ ውስጥ ነው ያለው" ብለዋል፡፡ እኛ (ኢዜማ) ግን ከዓመት ተኩል በፊት ነው ይህንን ነገር ደግመን ደጋግመን የነገርናቸው፡፡ ለውጡ መሬት እንዲወርድ ከተፈለገ ካድሬው ላይ መስራት አለብዎት ብለናቸው ነበር፡፡ እሳቸው ሕልውናውን የፈለጉት ይመስላል፤ ይህንን የካድሬ መዋቅር አልነኩትም፡፡ የሚሰጣቸውን ምክር ለመስማት በጎ ልቦና በማጣታቸው ወይም ተግባራዊ ባለማድረጋቸው እነዚህ ችግሮች ሊከሰቱ ችለዋል፡፡ እኔ ከላይ ያነሳኸውን ሀሳብ እደግፋለሁ፡፡ መንግሥት የዜጎችን ሰላምና ደሕንነት መጠበቅ እንዲሁም የሀገር ፀጥታ ማስከበር አለበት፡፡ በዜጎች ዘንድ አመኔታም የሚያገኘው ይህን ካደረገ ነው፡፡ አንድ መንግሥት በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብም ከበሬታን የሚያገኘው የዜጎቹን ደኅንነት፣ የሀገሪቱን ሰላምና ፀጥታ ማስከበር የቻለ እንደሆነ ነው፡፡

የተፈጠረውን ሁከትና ግርግር ተከትሎ በሰማናቸው አንዳንድ ክሶች ላይ ሕዝቡን አደራጅተው ሕዝቡ ራሱን እንዲከላከል አድርገዋል በሚል ክስ ሲቀርብ ሰምተናል፡፡ ሕዝብን መጠበቅ ያለበት መንግሥት፤ ሀገርን መከላከል፤ ንብረትን ከውድመት ማዳን ያለበት መንግሥት፤ ባለመከላከሉ ነው መጠየቅ ያለበት ወይስ መንግሥት ያንን ባለማድረጉ ዜጎች ራሳቸውን ለመጠበቅ መደራጀታቸው ነው ወንጀል?! ዜጎች ሳይደራጁ በሻሸመኔ ከተማ እንደሆነው በልጆቻቸው ፊት መታረድ ነበረባቸው? በሚስቶቻቸው ፊት መገደል አለባቸው?! ምንድነው እያሉን ያሉት? ወኔው



ካላቸው ሕዝቡን ወጥተው ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው! ሕዝቡ ይጠብቁናል ብሎ አመኔታ የጣለበት መንግሥት ሕዝብ ሲታረድ፣ ለሀገር ብሎ ያፈሰሰው መዋዕለ ንዋይ ሲወድም ያንን መከላከል ካልቻሉ መንግሥትነታቸው ምኑ ላይ ነው?! ከጠቅላይ ሚኒስትሩ አንስቶ እስከ ፖሊስ ድረስ ላሉት ዜጎች ሕዝቡ ደሞዝ እየከፈላቸው በምትኩ ግን አገልግሎት ማግኘት አልቻለም! ሕይወቱን እንኳ ሊታደጉት አልቻሉም! ይህ የሆነው ከአቅም በላይ ስለሆነ አይደለም! እርምጃ ሲወስዱ ከአቅም በታች እንደሆነ አይተናል፡፡ ያንን ያላደረጉት በራሳቸው ስሌት መሰረት ነው፡፡ ሀገሩን፣ ሕዝቡን እንዲሁም የሕዝቡን ንብረት መጠበቅ ባለመቻላቸው ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው! መንግሥት ከዚህ ወዲያ እንዲህ አይነት ስህተት እንዳይደገም መጠንቀቅ አለበት! ዜጎችም ከእንደዚህ አይነት አደጋ ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ወንጀለኞችም ራሳቸውን ለመጠበቅ በየቀበሌውና በየወረዳው ከፖሊስ ጋር በመቀናጀት ራሳቸውን መጠበቅ አለባቸው!

**መንግሥት ለሚነሳበት ትችት ሲሰነዝር የምንሰማው ምክንያት አለ፡፡ ከቀደመው ኢሕአዴግ የወረሰው መዋቅር ችግር እንደሆነበት፣ መዋቅሩ ፀድቶ እንዳላለቀና በመንግሥት መዋቅር ውስጥ የተሰገሰጉ የቀድሞ ስርአት አመለካከት ያላቸው ሰዎች ለውጡን ለመቀበል ፍቃደኛ ስላልሆኑና እንዲሁም ጠንካራ ተቋማት በሀገሪቷ ላይ አለመኖሩ ፈተና እንደሆነበት ያነሳል፡፡ ይህን አስተያየት እንዴት ይመለከቱታል? ይህ ምክንያትስ እየተፈጠሩ ላሉ ችግሮች ማሳበቢያ ምክንያት ሊሆን ይችላል?**

በተቻለኝ አቅም በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጫማ ውስጥ በመቆም ለመረዳት እሞክራለሁ፡፡ ሕመማቸውንም ለማዳመጥ እጥራለሁ፡፡ ነገር ግን ከሁለት ዓመት በላይ ሰጥተናቸዋል፡፡ ከዚህ ቀደም ብዙ ይቅርታ አደረግን፡፡ ሕዝቡም እንዲረዳቸውና እንዲሰክን ወትውተናል፡፡ ይህንን ያደረግነው አሁን የሚሏቸው ችግሮች እንዳሉ ስላወቅን ነው፡፡ ይሄንን በስንት ዓመት ነው የሚያስተካክሉት? ሁለት ዓመት ተኩል ማለት እኮ በሌላ ሀገር ሽግግር የሚደረግበት ጊዜ ነው፡፡ ችግሮቹ በአንዴ ጠርተው የሚያልቁ እንዳልሆኑ እንረዳለን፡፡ ነገር ግን ችግሮቹን ለመከላከል የተነሳሽነት ችግር ጠፍቷል፡፡ ቀላል ማሳያ ለማቅረብ፣ ሌላውን እንተወውና አዲስ አበባ ላይ እሳቸው ያሉበት ቤተመንግሥት 1 ኪሎ ሜትርና 500 ሜትር ርቀት ላይ ድሃ ሕዝብ በድንጋይ ሲደበደብ ነው የነበረው፡፡ አስለቃሽ ጭስ ሲተኮስ ነው ድንጋይ ሲወረውሩ የነበሩ ልጆች የተበተኑት፡፡ ብዙዎቹ ይህን ሲያደርጉ የነበሩት ልጆች ናቸው፡፡ በቁጣና በግልምጫ የሚመለሱ ናቸው፡፡ ሆን ተብሎ ሁከት ለመፍጠር የተፈለገ እስኪመስል ድረስ ትናንሽ ልጆች 30 እና 35 ኪሎ ሜትር አቆራርጠው ከተማ ውስጥ ገብተው እስኪረብሹ ድረስ መንግሥት ምን ይሰራል? ይህንን የሚከላከል የፖሊስና የሠራዊት ሀይል አልነበረም ወይ? ከሌለ በኋላ ላይ እንዴት ተከላከለ? ችግሮች እንዳይፈጠሩ ቀድሞ የመስራት ችግር ነው እንጂ፡፡

መዋቅራቸውን አፅድተው ጨርሰዋል ብለን ባናምንም የተፈጠረውን ችግር ከተሞች ዙሪያ እያለ ያ ሁሉ ንብረት ሳይወድም፣ የዜጎች ሕይወትም ሳይጠፋ መከላከል ወይም ጉዳቱን ማሳነስ ይቻል ነበር፡፡ በኦሮሚያ ለጠፋው ሕይወት ቀድመው ማስጠንቀቂያ መስጠት ትዕዛዝም ማስተላለፍ ይችሉ ነበር፡፡ ከክልሉ መስተዳድር ጋር ተነጋግረው ሀገሪቷ ያለችበትን ሁኔታ አይተው ሕዝቡ ራሱን እንዲከላከል ማድረግ ይችሉ ነበር፡፡ ለሊት ጀምሮ ነው ንብረት ሲወድም፣ ሕይወት ሲጠፍ የነበረው፡፡ እኛ የአርቲስት ሀጫሉን ግድያ ሳንሰማ ሌሎች ዜጎች ግን እየተገደሉ ነበር፡፡ በዚሁ ለሊት ይህ መረጃ ይደርሳቸው ነበር፡፡ ተጨማሪ ጥፋት እንዳይደርስና የዜጎች ሞት እንዳይከሰት ለማድረግ አቅሙ አልነበራቸውም፡፡ አሁን ለታሰሩት የከተማ ከንቲባዎች ማስጠንቀቂያ መስጠት አይቻልም ነበር ወይ? በአንዳንድ ከተሞች እኮ ሠራዊት ከነናቸው ነበር፡፡ለምሳሌ ሻሸመኔ ከተማ ከጎኑ ልዩ ሀይል ነበር፡፡ ያ ሀይል አልታዘዝም አለ? ምንድነው ችግሩ? በሕዝብ ግብርደሞዝ

የሚያገኘው ሠራዊት አልታዘዝኩም ብሎ ቁጭ ብሎ ነው፤ ሕዝብ በየቦታው ሲያልቅ የነበረው፡፡ ይህንን ሰራዊት በቀላሉ ማዘዝ ይችሉ ነበር፡፡ አላደረጉትም፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይቅርታ በመጠየቅ አይታሙም ለዚህ ተግባራቸው በይፋ ይቅርታ ቢጠይቁ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ አሁን የተፈጠረው ችግር ሞክረው ሳይሳካላቸው ቀርቶ አይደለም፡፡ ስላልሞከሩና ማድረግ የሚገባቸውን ስላላደረጉ ነው ችግሩ የተከሰተው፡፡

**ከዚሁ ከአርቲስቱ ግድያ ሳንወጣ የአርቲስቱ ግድያ ተከትሎ በመንግሥት በኩል ሕግ ለማስከበር ሲል የተለያዩ ዜጎችን በቁጥጥር ስር ማዋሉ የሚታወቅ ነው፡፡ "እስሩ የዘገየ ነው" የሚሉ ያሉ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ መንግሥት እስሩን እያካሄደ ያለው ሕግ ለማስከበር ብሎ ሳይሆን ይህን መልካም አጋጣሚ ተከትሎ በፖለቲካ የሚቀናቀኑትን ዋነኛ ተቀናቃኞችን ለማጥቃት ነው የሚሉም አሉ፡፡ እነዚህን ሁለት አስተያየቶች እንዴት ይመለከቷቸዋል?**

እኔ ታስሬ የማውቅ ሰው ነኝ፡፡ በታሰሩት ሰዎች ላይ ምንም አይነት አስተያየት አልሰጥም፡፡ አስተያየት ብሰጥ እንኳ ንፅህናቸውን በተመለከተ ነው፡፡ የትኛውም ሰው እስኪፈረድበት ድረስ ንፁህ ሆኖ የመቆጠር መብት አለው (Innocent Until Proven Guilty) የሚል መርሕ አለ፡፡ እውነቱ ምን እንደሆነ በማላውቅበት ሁኔታ ይህንን መርሕ ተላልፌ እነ እከሌ እነ እከሌ.... ቀድመው መታሰር ነበረባቸው ብዬ ፍርድ የምሰጥ ሰው አይደለሁም፡፡ የፍትሕ ስርአቱ እየተስተካከለ ካልሄደ ነገ ከነገ ወዲያ ሁላችንም እንደዚህ አይነት ዕጣ ሊደርሰን ይችላል፡፡ ከዚህ በፊትም ደርሶብን ያውቃል፡፡ ያጣነው ትልቁ ነገር ትክክለኛ ፍትሕ ማግኘት ነው፡፡ በሀገርህ ላይ አደባባይ መዋል በላ ልበልሃ ብሎ መከራከር በታሪካችን በባሕላችን የተለመደ ነው፡፡ መከሰስም ሞት አይደለም፡፡ መክሰስም የመጨረሻው ወንጀል አይደለም፡፡ ዋናው ግፍ የሚሆነው የፍትሕ ስርአቱ በሚገባው መሰረት ፍትሕን መስጠት ካልቻለ ነው፡፡ የሕግ ሂደት (Due Process of Law) መተግበር የማይቻል ከሆነና እንደ ከዚህ ቀደሙ ፍርድ ከቤተ መንግሥት የሚወጣ ከሆነ ትልቅ ጥፋት ነው፡፡ ሰዎች የተለያየ ግምት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ መንግሥትም የተለያየ እምነት ሊኖረው ይችላል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመሩት ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ክስ መስርቷል፡፡ ፍ/ቤት ፍርድ እንዲሰጥ እንጠብቃለን፡፡ እንደ ግለሰብ የራሴ አስተያየት አለኝ፡፡ (Innocent Until Proven Guilty) በሚለው አምናለሁ፡፡

ብዙዎቹ ወንጀሎች መንግሥት የሚጠየቅበት ይመስለኛል፡፡ ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት መንግሥት ሕዝብን መጠበቅ ነበረበት፡፡ ሕዝብም ለዓመታት አደጋ ሊፈጠር ስለሚችል መንግሥትን ጠብቀኝ ሲል ነበር፡፡ ፖለቲካ ፓርቲዎችም ወትውተዋል፡፡ ይህንን የቁራ ጩኸት አድርጎ ሕዝብንና ሀገሩን መጠበቅ ያልቻለው መንግሥት መጠየቅ አለበት፡፡ ይቅርታም መጠየቅ አለበት፡፡ የተከሰሱትን ወገኖች በሚመለከት የፍትሕ ስርአቱ ጥርስ አውጥቶ ከሆነ (ነፃ ነው አይደለም የሚለውን) እንደሚጠበቅበት መሄድ አለመሄዱን እኛም በቅርበት መከታተል እንፈልጋለን፤ እንከታተላለንም፡፡የሕግ ባለሙያዎቻችንን አማክረንም የምንሰጠው አስተያየት ይኖረናል፡፡ አሁን ላይ በዚህ ላይ ብገፋበት በሌላ ጊዜ መንግሥትን የምወቅስበትን ጉዳይ መድገም ነው የሚሆነው፡፡

**የፍትሕ ስርአቱን አሁንም አምርረው የሚተቹ አሉ፡፡ የቀድሞ ስርአት ቅጣይ ነው ይላሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች የሚያቀርቡት መከራከሪያም የአርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሣ ግድያ ተከትሎ የተካሄዱት እስሮች እንደከዚህ ቀደሙ ሁላ ማጣራት ያልተካሄደባቸው በጅምላ የተካሄዱ የጅምላ እስሮች ናቸው ይላሉ፡፡ ከጉዳዩ ጋር የተገናኘም ሆነ ያልተገናኘ ሰው ነው በቁጥጥር ስር እየዋለ ያለው፡፡ በቁጥጥር ሥር የዋሉ ዜጎችም በተናጠል ይሄን ይሄን በመፈፀም ነው የተጠረጠራችሁት ተብሎ ክስ እየቀረበባቸው አይደለም፡፡ በጅምላ ነው ክስ እየቀረበባቸው የሚገኘው፡፡ ፖሊስም በጊዜ ቀጠሮ ችሎት ተጨማሪ የጊዜ ቀጠሮ እንዲሰጠው የሚያቀርበው ምክንያት ተመሳሳይ እየሆነ ሳለ ፍ/ቤቶችም ተጨማሪ የጊዜ ቀጠሮ ከመስጠት አልተቆጠቡም፡፡ በፖሊስ በኩል የሚቀርበውን ወይም እየቀረበ ያለውን ክስ በመፈተሽ ይሄ ተጨማሪ የጊዜ ቀጠሮ አያስፈልገውም በማለት የተጠርጣሪዎችን ዋስ መብት ሲያከብሩ አይታይም፡፡ ፍ/ቤቶች አካባቢ ከአሁኑ ገለልተኛ ያለመሆን ፍንጭ ይታያል ይላሉ እነዚሁ ወገኖች፡፡ እርስዎ በዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

የተባሉት ነገሮች ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ ፍ/ቤቶች አሁን ሊፈተኑ ነው፡፡ የካድሬ መዋቅራቸውን ባለማፅዳታቸው ብዙ ችግር እንደተፈጠረ ሁላ በፍ/ቤት ደረጃ ሪፎርሙ በትክክል ሰርቷል ብሎ ከወዲሁ መናገር ሊከብድ እንደሚችል መገመት አይከብድም፡፡ ብዙ ዓመት የተበላሸ ሂደት



ነው፡፡ በውሸት መመስከርና በሀሰት ሰዎችን መክሰስ በፍትሕ አደባባይ ባሕል የሆነበት ሀገር መሆኑን እናውቃለን፡፡ ይህ በምን ያሕል መጠን ተሻሽሏል የሚለውን አሁን ከፍርዱ ጋር በተያያዘ ተጠግተን የምናየው ይሆናል፡፡ የፍትሕ ስርአቱ በአጭር ወራት ውስጥ ይስተካከላል ብለን አናምንም፡፡ የመንግሥት መዋቅር የተበላሸ እንደሆነ የምናየው የመንግሥት ኃላፊዎች ጭምር ሕዝብ ሲያልቅ ድምፃቸውን አጥፍተው አብረው ሲያስጨርሱ እንደነበር አይተናል፡፡ አሁን ያለው መንግሥት ውስጥ ንፁህዎቹ ሚኒስትሮችና ኃላፊዎች እነማን እንደሆኑ ለመናገር ይከብዳል፡፡ ይህን መዋቅር ለማስተካከል ጊዜ ያስፈልጋል ተብሎ እስካሁን ጠብቀናል፡፡ አሁንም ግን ገና ነው እየተባልን ነው ያለነው፡፡ በፍ/ቤት አካባቢ ያለው ነገር ተስተካክሏል ወይ ለሚለው ከግምት ከተነሳን የመስተካከሉ እድል ሩቅ ይመስላል፡፡ በሌሎች ነገሮች ላይ የሚታየው በፍ/ቤትም የሚደገም ከሆነ ብዙ ተስፋ ሰጪ አይሆንም፡፡ ለምሳሌ እኔ እስክንድር ነጋን ለመጠየቅ ወደ አዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን አምርቼ ነበር፡፡ የፖሊሶቹ ስነምግባር ደስ የሚል አይደለም፡፡ ሰዎችን ለመጠየቅ የሄዱ ሰዎችን በአግባቡ የማያስተናግዱ ስነ ምግባር የጎደላቸው ፖሊሶች ተመልክቻለሁ፡፡ ፍ/ቤትም የሚሰራው ከእንደዚህ አይነት ፖሊሶች ጋር ስለሆነ በአንድ ጊዜ የጠራ ነገር ላይኖር ይችላል፡፡ አሁን ላይ ባልተጨበጠ ነገር ከማውራት በቋሚነት ፍ/ቤትን የሚከታተሉ ጠበቆች ይኖሩናል፤ አሉንም፡፡ ጠበቆቻችን ሂደቱን በደንብ እንዲከታተሉ አድርገን የፍትሕ ስርአቱ ምን ላይ ነው? ምን ይጎለዋል? ምን ይቀረዋል? የሚሉ ነጥቦችን ገምግመን ነው አቋም የምንይዘው፡፡ አንዳንድ ደስ የማይሉ ምልክቶች ብናይም የፍርድ ሂደቱ ተንጠልጥሎ ባለበት ሁኔታ ብዙ መናገር ጥሩ





ነው ብዬ አላምንም፡፡ የተጠርጣሪዎችን ንፅህና እንደ መጠበቅ ሁላ በፍትሕ ስርአቱም በኩል አዎንታዊ ነገር ይሰራል ብለን እንጠብቅ፡፡ የፍትሕ ስርአቱ እንደጠበቅነው ካልሆነ በራሳችን የሕግ ባለሙያዎች አጣርተን ለሕዝብ ይፋ እናደርጋለን፡፡

የአርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳን ግድያ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተቀናቃኞቻቸውን ለማጥቃት እየተጠቀሙበት ነው፡፡ በሀሳብ ከእሳቸው የሚለዩ ፖለቲከኞች ለእስር እንዲዳረጉ ተደርገዋል፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አያያዝ እንደሚያመላክተው በአንድ ሰው አምሳል (በራሳቸው አምሳል) የሚመራ ፍፁም አምባገነን የሆነ አገዛዝ ለመፍጠር እየተንቀሳቀሱ ነው የሚል ሀሳብ ይነሳል፡፡ በዚህ ላይ አስተያትዎን ያጋሩኝ፡፡

በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት፣ የኢሕአዴግ ደመ ነፍስ ያለው መንግሥት ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ ኢሕአዴግ የሚለውን ስሙ እንደቀየረ ሁላ ተግባሩንም ለመቀየር እየሞከርኩ ነው እንደሚል እናውቃለን፡፡ ፍላጎቱ ከልብ ነው ወይስ ብዙ ወንጀል የተፈፀመበትን ፓርቲ ስም ይዘን ማሸነፍ አንችልም ብለው ነው ስም ቀይረው የመጡት የሚለውን አናውቅም፡፡ መሬት ላይ ያየናቸው አብዛኞቹ ነገሮች የድሮውን ኢሕአዴግ የሚመስሉ እነሱኑ የሚሸቱ ነገሮች ሲፈፀሙ እያየን ነው፡፡ ጥቂት ነገር ይዘህ ጥቅል ነገር ደምድመህ መሄድ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ቀደም ብዬ እንዳልኩህ የኢሕአዴግነት ባሕሪው በተለያየ መልኩ ይገለፃል፡፡ ይሄንን ነገር ተቃዋሚዎችን ለማጥቃት እየተጠቀሙት ሊሆን ይችላል፡፡ አያደርጉትም ብሎ መደምደም ያስቸግራል፡፡ ያደርጉታል ብሎ መቶ በመቶ እርግጠኛ ሆኖ ለመናገር በተጨባጭ ማስረጃ ሊኖር ይገባል፡፡ ተጠርጥረው የተያዙ ሰዎችስ ንፁህ ናቸው ወይ? በተቃናቃኝነታቸው ነው እየተጠቁ ያሉት ወይስ ወንጀል አለባቸው? የሚለውን መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡ የተቀጠፉት ነፍሶችም ሆነ የወደመው ንብረት በጣም ብዙ ነው፡፡ ይህ ያለማንም ባለቤትነት ዝም ብሎ ይፈጠራል ብለን አናስብም፡፡ ተጠርጥረው የተያዙት ሰዎች ናቸው ወንጀሉን የፈፀሙት ብሎ የመናገር ኃላፊነት የእኛ አይደለም፡፡ ፍ/ቤት እስኪፈርድባቸው ድረስ የእነሱንም ንፅሕና ማጉደፍ ተገቢ አይደለም፡፡ በተመሳሳይ መልኩ መንግሥት እነሱን ስለከሰሰ ሊያጠቃቸው እየሞከረ ነው ብለን ለመደምደም ኢሕአዴጋዊ ባሕሪው እንዳለ ብናምንም፣ በዚህ ልዩ ሁኔታ ከዚህ ሁላ ሂደት በኋላ መንግሥት አሁን ለማሰር የመረጣቸውን ሰዎች እነሱን ለማዳከም ስለፈለገ ነው የሚለው ላይ ቆይቶ አስተያየት መስጠት ይሻላል፡፡ በፍርድ ሂደቱ ላይ መንግሥት ተፅእኖ ካላደረሰና አሁን ተጠርጥረው የተያዙትን ሰዎች ፍ/ቤት ነፃ ካላቸው የመንግሥትን ፍላጎት (ተቃዋሚዎችን የማዳከም) ነው የሚለውን ያረጋግጥልናል፡፡

**ለውጡ ላይ አደጋ እንደተጋረጠበት እያየን ነው፡፡ አንዳንድ ልሂቃን ለውጡ ላይ አደጋ የተጋረጠው ወዴት እንደምናመራ የሚያመላክት ፍኖተ ካርታ አለመቀመጡ ነው ይላሉ፡፡ በሌላ በኩል ሌሎች አካላት ደግሞ ሁሉን አቀፍ ውይይት ባለመካሄዱ የተነሳ ነው ይላሉ፡፡ እነዚህ ሁለት ሀሳቦች ላይ ምን ሀሳብ አሎት?**

ወደኋላ መለስ ብለን ችግሩን ካየነው የስልጣን ግብግብ (Power Struggle) ያለበት ይመስለኛል፡፡ ግብግቡ ከለውጡ በኋላ ነጥሮ የበላይ ሆኖ ለመውጣት ነው፡፡ ሲብላላ የነበረ መገፋፋት ነው የነበረው፡፡ የዛን ውጤት እያየን ያለን ነው የሚመስለኝ፡፡ ግብግቡ እንደተባለው በውይይት እልባት እንዲያገኝ እድል አልተሰጠውም፡፡ እዚህ ግባ የሚባል የመወያያ መድረክም አልነበረም፡፡ ይህ መገፋፋትም ውጥረቱን ሳይጨምረው አልቀረም፡፡ መሰረቱ ግን ስልጣኑን ለመያዝ የሚደረግ ግብግብ ነው፡፡

ታዝበህ ከሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሰሞኑ ለውጡን እንዴት እንዳመጡት ሲናገሩ ነበር፡፡ እኔ እሳቸውን ብሆን አልናገርም፡፡ 30 ዓመታት የኢሕአዴግ አባል ሆኖ ሕዝብ ላይ ቀምበር ጭነው አብረው ሲገርፉ፣ ሲያስገድሉ የነበረውን ሕዝብ..... ሕዝብ እምቢ ብሎ ቀምበሩን ሰብሮ ነፃ ሲወጣ ቀኝ ኋላ ዞር ብለው የመጡ ሰዎች የመፍትሔ ሁላ ባለቤት፣ የሀሳብ ሁላ ምንጭ አድርገው ራሳቸውን ሲወስዱ ቅር ያሰኛል፡፡ "መስታወት ቤት ውስጥ ያለ ሰው ድንጋይ አይወረወርበትም" እንደሚባለው ዝም ቢሉ ጥሩ ነበር፡፡ የለውጡም ሆነ የስልጣን ባለቤትነት ስሜት አለ፡፡ ሀገራዊ መግባባቱ እየጨመረ እንዲሄድ የሚያደርግ ነገሮች ባለመኖራቸው ለችግሮች መፈጠር አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ሆደ ሰፊነትና ነገን አርቆ ማየት ከሌለ በስተቀር ስልጣኑን እስከትይዘው ድረስ ሽኩቻው ሊቀጥል ይችላል፡፡ ነገሮችን ለማርገብየነበሩት ውይይቶች በቂ ናቸው ብዬ አላምንም፡፡ በሆደ ሰፊነት መወያየት፣ መቀራረብና መምከሩ የተሻለ ነው፡፡ ሩቅም የሚወስደን እሱ ነው፡፡

የሕግ የበላይነት እየተከበረ መሄድ አለበት፡፡ በእንደዚህ አይነት ስስ ነገሮች ላይ ግን እስር መፍትሔ አይሆንም፡፡ ጉልበትና እስር መፍትሔ ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያ እስካሁን ብዙ ትጠቀም ነበር፡፡ ምክንያቱም ብዙ ሰዎች ተገድለዋል፤ ታስረዋል፡፡ በእነሱ ሞትና እንግልት ጥሩ ነገር ሊሰራ ይችል ነበር፡፡ የመፍትሔው ቁልፍ የሚመስለኝ ወደ ውይይት ወደ መመካከር መምጣት ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን ውይይት በሚል ማንም እንደ ፈለገ ሀገር የሚያፈርስበት ሁኔታ መፈጠር የለበትም፡፡ሰጥቶ መቀበል ያለበት ልባዊ የሆነ የውይይት መድረክ ነው የሚያስፈልገው፡፡ ኢትዮጵያ ትልቅ ሀገር ነች፡፡ የተወሰኑ የኢሕአዴግ አባላት የነበሩ ሰዎች ብቻ እንደለመዱት የሚዘውሯት አይደለችም፡፡ ገና ከእስር እንደተለቀኩ ያልኩት ነገር ነበር፡፡ የዚህችን ሀገር ችግር ለመፍታት ሁላችንም ተሰባስበን እንኳ አንበቃም፡፡ ጥቂት ሰዎች ብቻ ከጳጳሱ በላይ ለመሆን አትሞክሩ እያሉ የሚቀጥሉበት ሁኔታ እንዳይመጣ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ የውይይት በሮችንም ማስፋት ያስፈልጋል፡፡ ቁስላችንን የሚያሽረው እሱ ነው፡፡ በእስርና በግድያ የሀገር ሰላም ሊጠበቅ አይችልም!

**መፍትሔው ውይይት ነው ካሉኝ፡፡ በውይይት ሂደት ደግሞ ሰጥቶ መቀበል ግድ ይላል፡፡ መንግሥት ሰጥቶ ለመቀበል ዝግጁነቱ አለው ብለው ያምናሉ?**

ወጣ ገባ የሚሉ የመንግሥት ባሕሪያት እያየን ነው፡፡ ሁላችንም የደገፍናቸው በጎ ጅምሮች ነበሩ፡፡ ለጠቅላይ ሚኒስትሩም ብዙ አክብሮት ለግሰናቸዋል፡፡ ይህንን ስናደርግ ስማችን ጭቃ ሲቀባ ነበር፡፡ የፓርቲያችንን ሕልውና እየጎዳን ጭምር ነው ይህን ያደረግነው፡፡ ፓርቲያቸውን (ብልፅግናን) የማሻገር ሕልም ብቻ ተሸክመው ሲጓዙ የነበረ ባሕሪያቸው እየጎላ ሲመጣ አይተናል፡፡

ምሳሌ ለማቅረብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠቅላይ

ሚኒስትር ሆነው ሳለ (ናቸውም ብለን ተቀብለናቸው ሳለ) ጠዋትም ማታ በየሚዲያው (ፋና፣ ዋልታ፣ ኢቲቪ፣ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ) ብልፅግና ብልፅግና ሲሉ ነው የነበሩት፡፡ አብረን ሀገር እናሻግራለን ብለን ሳለ እሳቸው ብልፅግናን ለመሸጥ ሲሞክሩ ሳይ አዝናለሁ፡፡ እኛ (ኢዜማ) ፓርቲያችንን ሳይሆን ሀገርን እናስቀድማለን፤ ዋናው የዴሞክራሲ መንገድ ይጠረግ እንጂ ስንል ነበር፡፡ ብዙ ሰዎችም እነዚህ ሰዎች ምን እያሉ ነው እያሉ ይወቅሱን ነበር፡፡ ቀኑ በገፉ ቁጥር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለዴሞክራሲ ቁርጠኝነት አያሳዩም፡፡ እሳቸው ሀገር ሲያሻግር ማየት የሚፈልጉት የራሳቸው ፓርቲን ብቻ ነው፡፡ መጀመሪያ ካየንባቸው በጎ ፍቃድና ኢትዮጵያ ላይ ለዘመናት ጨልሞ የነበረውን ጨለማ ገፎ ኢትዮጵያን የብርሀን ሀገር ለማድረግ ወይንም የዴሞክራሲ ጮራ የሚወጣበት ሀገር ለማድረግ የገቡትን ቃል ይተገብሩታል የሚለው ነገር ላይ በግሌ እንድጠራጠር እየሆንኩ ነው፡፡ ከመንግሥት የሚጠበቀውን ቁርጠኝነት እያየሁ አይደለም፡፡

**በብልፅግና ፓርቲና በሕወሓት መካከል እየተደረገ ያለ የቃላት ጦርነት አለ፡፡ በሁለቱ ፓርቲዎች መሀል ያለው ችግር እንዴት ሊፈታ ይችላል?**

ሁለቱም (ብልፅግናም ሕወሓትም) የኢሕአዴግ ሽርፍራፊዎች ናቸው፡፡ ሀገር እናስተዳድራለን ብለው ኢትዮጵያን ቁም ስቅሏን ሲያበሏት ነበር፡፡ እሱን ምዕራፍ መሻገር እንፈልጋለን፡፡ ቁስል ማከክ አንፈልግም፡፡ ይቅርታ፣ መቻቻልና የጋራ ራዕይ ያስፈልጋል፡፡ ሀገርን ትውልድን ታሳቢ አድርጎ መሄድ የኢትዮጵያውያን የአላማ ሰንደቅ መሆን አለበት ብለን እናምናለን፡፡ "ያደቆነ ሰይጣን ሳያከስ አይቀርም"እንደሚባለው ይህ ባሕሪያቸውና የነበሩበት ነገር ኢትዮጵያን ችግር ውስጥ እየከተታት ነው ያለው፡፡ችግር የሚታየው በመንግሥት በኩል ብቻ ነው ማለት በቂ አይደለም፡፡ በሕወሓትም በኩል ሕግና ስርአትን ያለመከተል ነገር ይታያል፡፡ ሀገርን በሚያክል ጉዳይ ላይ የልጆች ጨዋታ ሲጫወቱ ይታያል፡፡ እልህ ሲጋቡም እናያለን፡፡ በሁለቱም በኩል ይህ መስተካከል፤ መርገብ አለበት፡፡ በደንብ ይተዋወቃሉም፡፡ ስትተዋወቅ የመክረር ነገር እንዳለ ይታወቃል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሁለቱም ሁለተኛ እድል እንደሰጣቸው ማወቅ አለባቸው፡፡ እንደ ዘውዱ ስርአት ተፈነቃቅለው የመውደቅ፣ የመገደልና መታሰር ሊከተል ይችል ነበር፡፡ ሕዝቡ ከዛ ሁሉ ግፍና መከራ በኋላ



‹‹ ይህ የዘር ትርክት በተበላሸው የፖለቲካ ባሕላችን ላይ ሌላ መከራ ጨምሮብናል፡፡ ባልዘመነ ፖለቲካ ላይ ዘረኝነት ሲጨመርበት ምን አይነት መከራ ሊያመጣ እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ በልቶ ያልጠገበ ሕዝብ እንደ እሱ በልቶ ያልጠገበውንና ከጎኑ የሚገኘውን የሚያርደው በሌላ ምክንያት የተነሳ አይደለም፡፡››

ሁለተኛ እድልን መስጠትን ነው የመረጠው፡፡ አሁንም ግን ሕዝብን እንደ ሳርና ቅጠል እየቆጠሩ ነው፡፡ በተለይም በሕወሓት በኩል የሚደረገው ፉከራና ቀረርቶ ተገቢ አይመስለኝም፡፡ ወደ ልቦናቸው መመለስ አለባቸው፡፡ እስካሁን በጠፋው ሕይወት፣ በወደመው ንብረት ሀገር በብዙ መልኩ እንደተጎዳች ያውቃሉ፡፡ ሕዝቡ ይህን ሁሉ ባይረሳም ይቅር ለማለት ዝግጁ ነው ብለን እናምናለን፡፡ ይህ እድል ባያመልጣቸው ጥሩ ነው፡፡ በተለመደው መገናተር ሀገራችንን ወደማያስፈልግ ነገር ውስጥ በመክተት ሌላ መከራ ባያመጡና ደሃውን ሕዝብ ዳቦ ማብላት ተገቢ ሆኖ ሳለ አጠገቡ ለማይቆሙ ነገር በጥይት እንዲሞት መፎከር ተገቢ ነው ብለን አናምንም፡፡ እውነቱን ለመናገር ከሕወሓት ጋር በተያያዘ መንግሥትን አላማውም፡፡ መሳሪያ አለ፤ ሰራዊት አለ፤ ስልጣኑም እኔ ጋር ነው ብሎ ብዙ ሰዎች ግፊት ሲያደርጉ እንደነበረው ትግራይ ላይ ሄዶ ጦርነት በመክፈት ለማስተንፈስ የሞከረው ነገር የለም፡፡ ነገሩን በትዕግስትና በመቻቻል ለማሳለፍ እየሞከሩት ያለው ነገር የሚያስመሰግን ነው፡፡ መሳሪያ አለን ብለው ዘለው ቢገቡ ብዙ ንፁሃን ዜጎች የሚያልቁበት ነገር ይፈጠር ነበር፡፡ እሳቱ እዚህም ያሉትንም ሆነ እዛ ያሉትን አይነካቸውም ነበር፡፡ ከዚህ አንፃር እኔ የምወቅሰው ሕወሓትን ነው፡፡ በመንግሥት በኩል የሚቀረው ነገር ልቦናውን አስፍቶ የወንድ በር በመስጠት ከልብ መወያየትና ከልብ ለመደማመጥ መሞከርና በፖለቲካ ጥበብ አሸንፎ መውጣትን ነው፡፡ በውይይት ችግሩን ቢያረግቡትና ሀገራችንን ሌላ የችግር አረንቋ ውስጥ ላለመክተት ቢጠነቀቁ ጥሩ ነው፡፡ በሰላማዊና በውይይት ችግሩ መፈታት አለበት፡፡ ሕወሓት እስካሁን ሲያደርገው የነበረው ነገር በጣም የበዛና የከፋ ነው፡፡ ይህ ማንአለብኝነት መቆም አለበት፡፡ ትግራይ የሁላችንም ሀገር ነው፡፡ የእነሱ ሀገር ብቻ አይደለም፡፡ የትግራይ ሕዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተለየ አይደለም፡፡ በሁለቱ ፓርቲዎች ችግር ምክንያት ሀገር መፍረስ የለበትም፡፡ የፓርቲ ባለስልጣናት ስለተጣሉ ሕዝብ አይጣላም፡፡ ሁለቱም ፓርቲዎች ወደ ልቦናቸው እንዲመለሱ አደራ እላለሁ፡፡ ጥሪዬንም አቀርባለሁ፡፡

**ኢዜማ ሐምሌ 6 ቀን 2012 ዓ.ም ባወጣው መግለጫ ላይ አሁን ላይ እየተፈጠሩ ላሉ ችግሮች ዘውግና ሀይማኖትን መሰረት አድርገው የሚሰበኩ የፖለቲካ ትርክቶች አስተዋፅኦ አድርገዋል ብሏል፡፡ በሌላ በኩል የፖለቲካ ችግሮቻችን መንስኤ የልሂቃን አለመግባባትና ለውይይት ዝግጁ አለመሆንና ችግሮችን በጠረጴዛ ዙሪያ ለመፍታት ዝግጁ አለመሆን ነው ብለው የሚያነሱ አሉ፡፡ በእርስዎ ዕይታ የፖለቲካ ትኩሳቶቻችን መንስኤዎች ምንድን ናቸው? ከችግሮቻችን መውጫ መንገዱስ ምንድን ነው?**

ከባድ ጥያቄ ነው፡፡ በቀላሉ የሚመለስ አይደለም፡፡ ጥያቄህን ለመመለስ ልሞክር፡፡ ለእኔ የችግራችን ሁሉ ምንጭ የሚመስለኝ የፖለቲካ ባሕላችን ነው፡፡ በፖለቲከኞቻችን መካከል የሚታየው ግብግብ ስታይ፣ እሳቤያችንን ስትመለከት ታሪካችን ውስጥ ታገኘዋለህ፡፡ አሁን እየተፈጠረ ያለው ነገር ልክ በዘመነ መሳፍንት የነበረችውን ኢትዮጵያ መልሶ የመፍጠር አይነት ሂደት ነው፡፡ ዘመኑ ከእኛ ቢርቅም አስተሳሰቡ ግን ለእኛ ቅርብ ነው፡፡ በዛ አይነት ስሌት ውስጥ ነው የምናድገው፡፡ ኢትዮጵያውኖች ለመነጋገር ከባድ የሚሆንብን ከየትም ከመጣ ባሕሪያችን አይደለም፡፡ ከባህላችን ከሚመነጭ እንጂ፡፡ ማንበርከክም ሆነ መንበርከኩ ከየትም የመጣ አይደለም፡፡ ከጦረኝነት ባሕላችን ነው የሚመነጨው፡፡ ብዙ ጊዜ በመሳሪያ ስንከራከር እንጂ በአንደበት ስንከራከር አላሳለፍንም፡፡ ለስልጣን ነው ስንታገል የነበረው እንጂ ሕዝብን እንዴት እናልማው ስንል አይደለም የቆየነው፡፡ የድሮ ነገስታቶቻችንን ታሪክ ከተመለከትን በድርቅና በወረርሽን የተጎዳን ሕዝብ እያሰለፉ እርስ በእርሳቸው ስልጣን ለመያዝ ሕዝቡን ሲያጋድሉ ነው የነበሩት፡፡ አሁንም ያለውን ግብግብ ስታጤነው ተመሳሳይ ነው፡፡ መለስተኛ የሆኑ የጦር አበጋዝ አይነት እየተፈጠሩ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በታሪካችን ውስጥ ወደኋላ ሄደህ የምታየው ነው፡፡ በያ ትውልድ ውስጥ የነበረው ከመሰዳደብ አንስቶ እስከ መገዳደል የነበረው ባሕል ከየትም የመጣ አይደለም፤ ከፖለቲካ ባሕላችን እንጂ፡፡ ትልቁ ችግር የፖለቲካው አለመዘመን ነው፡፡ አለባበሳችንና አናናሯችን በተወሰነ መልኩ ዘመናዊ ቢመስልም የተሰራንበት አስተሳሰብ ግን በጣም ኋላ ቀር ነው፡፡ የውይይትም ሆነ የመነጋገር ባሕል የለም፡፡ ሁልጊዜ ራስን ማጀገን እና ሌላውን ማኮሰስ እንዲሁም ይዋጣልን የማለት ነገር ነው ያለው፡፡ ይህ ይመስለኛል ዋነኛው ችግራችን፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ በመግለጫችን ላይ እንደጠቀስነው ይህን ሁሉ ኋላ ቀር የሆነ አስተሳሰባችንንና የፖለቲካ ስሜታችንን ማስተካከያ ተደርጎ እንደ ብቸኛ መፍትሔ የተወሰደው በተለይም ላለፉት 40 ዓመታት ነገሮችን በዘር ትርክት ማየት ነው፡፡ ይህ የዘር

‹‹ . . . ሌላው ጋር ችግር አለ እንደምንለው ሁሉ እኔም ጋር የሚጎድል ነገር አለ ብሎ ማሰብና በሚያመዛዝንና ምክንያታዊ በሆነ አዕምሮ ነገሮችን ለመረዳት በመሞከር ትውልድን አሻግሮ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡››

ትርክት በተበላሸው የፖለቲካ ባሕላችን ላይ ሌላ መከራ ጨምሮብናል፡፡ ባልዘመነ ፖለቲካ ላይ ዘረኝነት ሲጨመርበት ምን አይነት መከራ ሊያመጣ እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ በልቶ ያልጠገበ ሕዝብ እንደ እሱ በልቶ ያልጠገበውንና ከጎኑ የሚገኘውን የሚያርደው በሌላ ምክንያት የተነሳ አይደለም፡፡ እንደ እሱ ኑሮውን ለማሸነፍ የሚውተረተረውን ሕዝብ የሚገለው በዘረኝነት ለ30 ዓመታት ስለተሰራበት ነው፡፡ ሌላ አይደለም፡፡ ራሱ የሚበላበትን ሕንፃ የሚያቃጥለው ሕዝብ በምን አይነት ዘረኝነት ስሪት ውስጥ እንዳለፈ ፖለቲካን የሚረዳበት፣ ዜግነትን የሚያይበት ትርክት በጣም የተሳሳተ እንደሆነ ታያለህ፡፡ ችግሩን የዘር ፖለቲካ ውስጥ ታገኘዋለህ፡፡ በዋናነት የዘር ፖለቲካ ነው እየጎዳን ያለው፡፡ አንተ የሆነ ዘር አካል ስለሆንክ ንፁህ ሌላው ደግሞ ከአንተ የተሻለ ንፁህና በጎ አሳቢ ቢሆንም የሌላ ብሔር አባል ስለሆነ ሀጢአተኛ ወይም ሴጣን ተደርጎ በግ እንኳ ለማረድ የማትጨክነውን ያሕል እሱ ላይ የምትጨክንበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ የችግራችን መንስኤ ባለፉት 30 ዓመታት የነበረው የዘር ፖለቲካና ኋላ ቀር የሆነው የፖለቲካችን ውጤት ይመስለኛል፡፡ እነዚህ በጣም ኋላቀር የሆኑ የፖለቲካ አስተሳሰቦች (አንዳንዶቹ ደመ ነፍሳዊና እንስሳዊ የሆኑ ናቸው) ውይይትን ታሳቢ ማድረግ አለባቸው፡፡ መረዳዳት በጣም ወሳኝ ነው፡፡ እንደዚህ አይነት የእብደት ዘመን በእድሜዬ አይቼ አላውቅም፡፡ ወደፊትም ላይኖር ይችላል፡፡ ብዙሃን ያበዱበትን ይህን የእብደት ዘመን በመረጋጋትና ከራስ ጋር በመነጋገር፣ ከመናገር በፊት ማሰብ፣ ከማድረግ በፊትም ማሰብ፣ በሌላው ጫማ ውስጥ መቆም፣ የሌላውን ቁስል ለማዳመጥ መሞከር፣ ሌላው ጋር ችግር አለ እንደምንለው ሁሉ እኔም ጋር የሚጎድል ነገር አለ ብሎ ማሰብና በሚያመዛዝንና ምክንያታዊ በሆነ አዕምሮ ነገሮችን ለመረዳት በመሞከር ትውልድን አሻግሮ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ ሁላችንም ነገ አላፊ ነን፡፡ እንሞታለን፡፡ ልጆቻችን እኛ ባለፍንበት መከራ ማለፍ የለባቸውም፡፡ ስለዚህ ለእነሱ የተሻለ ሀገር ማውረስ አለብን፡፡ በትውልድ ፊት የሚያኮራ ነገር ጥለን ማለፍ አለብን፡፡ እሱን ደግሞ የማድረግ አቅሙ አለን፡፡ ችግሩ ተቀራርበን አለመነጋገራችንና አለመደማመጣችን ነው፡፡ የመስከን ችግር ነው ያለብን፡፡ ሁላችንም ብንተሳሰብና ብንደማመጥ ነው የሚሻለው፡፡

የብሔር ፖለቲካ ያዋጣል ብሎ ሰው ካመነ ለእኔ ችግር አይሆንብኝም፡፡ እሱን ግን ሕዝብ እንዲፈርድ መተው ያስፈልጋል፡፡ የእኔም አስተሳሰብ የእሱን ያሕል ክብር እንዳለው፣ እኔ እሱን ማዳመጥ እንደሚገባኝ ሁሉ እሱም እኔን ለማዳመጥ እድል የሚሰጥ የሰለጠነ አእምሮ ሊኖረን ይገባል፡፡ መደማመጥ ከቻልን ችግሮቻችንን መፍታት እንችላለን፡፡ መንገዱ ያ ነው፡፡ መንግሥትም ለውይይት በሩን መክፈት አለበት፡፡ ውይይቱ"እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው" አይነት መሆን የለበትም፡፡ በስነ ስርአት መደማመጥ ያለበት ውይይት ነው መሆን ያለበት፡፡ ሀገርን የሚያሻግር የልብ ውይይት ነው የሚያስፈልገን፡፡ በአባይ ግድብ እየተኮፈስን ነው አይደል? ከብዙ አባዮች በላይ የላቀው ታሪክ ዴሞክራሲ ነው፡፡ ለሺ ዓመታት የሚመጡ ትውልዶች የሚመሩበትን ስርአት ሰርቶ ማለፍ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ደግሞ በይስሙላ (እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው) ብለህ የምትሰራው አይደለም፡፡ ከልብ ተዘጋጅተህ ከልብ አምጠህ እንደ አንድ ሀገር ልጆች ተመካክረህ የምትሻገረው ምዕራፍ ነው፡፡ አዲስ የምትከፍተው የታሪክ ዘመን ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ በሁላችንም ዘንድ ዝግጅት ያስፈልጋል፡፡

**ለጊዜዎት በጣም አመሰግናለሁ!**

እኔም አመሰግናለሁ!

# በኢዜማ ምክትል ሊቀ መንበር የተመራ ግብረ ሀይል በአዲስ አበባ ከተማ ህገወጥ የመሬት ወረራ ተካሂዶባቸዋል የተባሉ ቦታዎችን ተዘዋውሮ ተመለከተ።



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በአዲስ አበባ የተለያዩ ቦታዎች ህገወጥ የመሬት ወረራ እየተካሄደ መሆኑን የሚያመላክቱ በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በደረሰው ጥቆማ መሰረት በፓርቲው ምክትል ሊቀመንበርና የግብረ ሀይሉ ሰብሳቢ ጫኔ ከበደ(ዶ/ር) የተመራ ቡድን ወረራው ተካሂዶባቸዋል የተባሉ ቦታዎችን ተዘዋውረው ተመልከተዋል ::

ለኢትዮጵያ ዜጎች ማህበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በርዕሰ ከተማዋ አዲስ አበባ እየተካሄደ ያለው የመሬት ወረራ ከእለት ወደ እለት እየጨመረ መምጣቱንና በተለያዩ የአዲስ አበባ ከተማ አካባቢዎች ከሚኖሩ ነዋሪዎች እየጨመረ የመጣውን የህገወጥ መሬት ወረራ ጥቆማ መሰረት በማድረግ ስራ አስፈጻሚው የጉዳዩን አሳሳቢነት በመረዳት በከፍተኛ የስራ አስፈጻሚ አባላት የሚመራ ግብረሀይል አቋቁሞ የተለያየ ስራዎችን ሲሰራ የቆየ ሲሆን በደረሰው ጥቆማ መሰረትም ግብረሀይሉ በንፋስ ስልክ ላፍቶ፣አቃቂ ቃሊቲ፣ቦሌ እና የካ ክፍለ ከተሞች በመዘዋወር የተባሉትን ቦታዎች የተመለከተ ሲሆን በከተማዋ እየተካሄዱ ባሉ አጠቃላይ ክንዋኔዎች ዙሪያ የደረሱትን ለህዝብ ይፋ እንደሚያደርጉ ጫኔ ከበደ(ዶ/ር) ለዜጎች መድረክ ገልፀዋል፡፡

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በቅርቡ በሀገራችን በተከሰቱ ወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ የፓርቲው ሊቀመንበር የሺዋስ አሰፋ « አዲስ አበባ ውስጥ ከአዲስ አበባ ውጪም ባሉ ከተሞችም በተለያዩ ቦታዎች ከፍተኛ የመሬት ወረራ እንዳለ ለፓርቲአችን በርካታ ጥቆማዎች መጥተው ነበር ይህንንም ተከትሎ የኢዜማ ስራ አስፈጻሚ ይህንን የሚከታተል ኮሚቴ አቋቁሟል፡፡ጥቆማዎችንም ተቀብሏል፡፡ይህንንም ለማድረግ የፈለግንበት ምክንያት ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ እንደገለፅነው ሀገርን በሚረጋጋ ስርዓት ባለው በእውነት ላይ በተመሰረተ ሁኔታ ነው መሄድ ያለብን ከሚል ፅኑ እምነት ነው፡፡ይህንን በተመለከተ ኮሚቴው ሰፊ ግዜ ተንቀሳቅሷል በርካታ የፅሁፍ የፎቶግራፍ የቪዲዮ ማስረጃዎችን አግኝቷል፡፡በተለይ በአራቱ ክፍለ ከተሞች ከፍተኛ የመሬት ወረራ መኖሩን በጣም ብዙ ማስረጃዎች መጥተዋል፡፡ከዜጎች የሚመጡትን ብቻ ሳይሆን ደብዳቤ ለከንቲባ ጽ/ቤት፡ለቤቶች ልማትና ለመሬት አስተዳደር ደብዳቤ ፅፈን ምላሽ እየጠበቅን እንገኛለን፡፡ኮንዶሚኒየምን በተመለከተም ዕጣ ያልወጣላቸውና ምዝገባ ለሌላቸው እንደተሰጠ በተጨባጭ ማስረጃዎች ደርሰውናል፡፡ 40/60 ቤቶች ሙሉ በሙሉ ክፍያ ከፍለው ቤት እንዳልተሰጣቸው አረጋግጠናል፡፡የመሬት ወረራዎቹ በዚህ ሰዓትም ተጠናክረው መቀጠላቸውን አረጋግጠናል በቅርቡ በተጨባጭ ችግሮቹን በሚቀርፍ መልኩ ለህዝቡ ይፋ እናደርጋለን »ማለታቸው አይዘነጋም፡፡





# “በወቅቱ በነበረው ግርግር ብዙ ሰዎች ወደ እስር ቤት ሊገቡ የሚችሉበት እድል ሰፊ ነው”

## ጠበቃ በሱ ፍቃድ ፋንታዬ



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል እና የሙያ ማኅበራት ተጠሪ ሒሩት ክፍሌ ከዚህ ቀደም ፍርድ ቤት ቀርበው መርማሪ ፖሊስ የሰራውን መዝገብ ሪፖርት ለፍርድ ቤቱ በማቅረብ በተጠርጣሪዋ ላይ የሰውም የሰነድም ምስክር እያዘጋጀ መሆኑን በተጨማሪም አፈላልጎ የሚያቀርባቸው ምስክሮቹም እንዳሉ በማሳወቅ ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠው በጠየቀበት ወቅት የተከሳሽ ጠበቃ ለምርመራ ከበቂ በላይ ጊዜ እንደተሰጠ በተሰጣቸው ቀን ሰርተው ማጠናቀቅ ስላልቻሉ ደንበኛቸው በዋስ ሊለቀቁ እንደሚገባ ለችሎቱ አስረድተዋል፡፡ መርማሪ ፖሊስ በበኩሉ ቢለቀቁ ማስረጃ ያጠፉብናል በማለት ተጨማሪ ጊዜ ቀጠሮ እንዲሰጠው ፍርድ ቤቱን በመጠየቁፍርድ ቤቱም መዝገቡን ተቀብሎ በማየት የቀራቸውን አጠናቀው እንዲያቀርቡ ተጨማሪ 8ቀናትን መስጠቱ ይታወቃል፡፡

ሒሩት ክፍሌ መርማሪ ፖሊስ በጠቀሰው ቦታ እንዳልነበረች ለዚህም ማስረጃ እንዳላት ማሳወቋን የጠቀሱት ጠበቃዋ ከማታውቀው ግለሰብ ጋር በአንድ ፋይል መከሰሷም ግራ እንዳጋባቸው ገልጸዋል፡፡ ፍርድ ቤት፣ አቃቤ ህግና ፖሊስ በነጻነት ይሰራል ብለን እንገምታለን፡፡በሀሰት የተወነጀለችው ለማለት በእሷ ላይ የሚቀርበውና ማስረጃ በማየትና በሚቀርቡ ምስክሮች ላይ ጥያቄ ሰንዝረን ከተከራከርን በኃላ የምናውቀው ሲሆን ቀጣዩ ቀጠሯችን የመጨረሻ ይሆናል ብለንም እናምናለን ብለዋል፡፡
በወቅቱ ተከስቶ በነበረው ግርግር ብዙ ሰዎች ወደ እስር ቤት ሊገቡ የሚችሉበት እድል ሰፊ ነው፡፡በመንግሥት በኩል በዛ ጊዜ እያንዳንዱን ስራ በጥንቃቄ መስራት የሚቹልበት ስላልነበረ በነበረው አስደንጋጭ ግርግር ሳቢያ ነው የገባችው የሚለው ትልቅ እድልን ይወስዳል፡፡ ወቅቱ የግርግር ስለሆነ ማንም ከማን ሊለይ በማይችልበት ወቅት መያዛቸውሰላም ለማምጣት ይሆናል የሚል ሰፊ እሳቤ ነው ያለን በማለት የሒሩት ክፍሌ ጠበቃ በሱ ፍቃድ ፋንታዬ ለዜጎች መድረክ አሳውቀዋል፡፡

ኢዜማ የሥራ አስፈጻሚዋን ሒሩት ክፍሌን የዕለት እንቅስቃሴዋን ትኩረት ሰጥቶ እየተከታተለ ሲሆን ከዚህ በፊትም “የዜጎችን ደህንነት የማስጠበቅ ዋነኛ ኃላፊነቱን ሳይወጣ ቀርቶ በዜጎች ሕይወት እና ንብረት ላይ ለደረሰው ጉዳት መንግሥት ለተጎጂዎች እና ለኢትዮጵያዊያን በሙሉ በይፋ ይቅርታ ይጠይቅ!” በማለት ይፋዊ መግለጫ ማውጣቱ ይታወቃል፡፡